በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-203260

ቀን፡-30/03/2014ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- የጉምሩክ ኮሚሽን ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

ተጠሪ ፡- አቶ ኤልያስ ዩሱፍ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲቻል ለማስፈቀድ የቀረበ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ግራ ቀኙ በነበራቸው ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ/ቁጥር 13393 ላይ በቀን 27/02/2012 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ዉሳኔዉ ከተነበበ በኋላ ተጠሪ በዉሳኔዉ ላይ በአሃዝና በፊደል የተጻፈዉ የገንዘብ መጠን ልዩነት ስላለበት ይታረምልኝ በማለት አመልክተዉ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ላይ በቀን 18/03/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፊደል "ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንትም ተብሎ የተጻፈዉ የአጻጻፍ ስህተት ስለሆነ አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም " ተብሎ እንዲነበብ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት አርሚል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት በቀን 11/01/2013ዓ/ም የተጻፈ ማመልከቻ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በማመልከቻዉ ላይ የጠቀሰዉ ምክንያት የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ያለፈበት በውሳኔዉ ላይ እርማት ሳይሰጥ በመቆየቱ ግልባጭ ሳይደርሰዉ ለ21 ቀናት በስር ፍርድ ቤት እንዲቆይ በመደረጉ ምክንያት ነዉ ስለሆነ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው መቆጠር ያለበት እርማት ተደርጎ ውሳኔው ከተሰጠበት ከቀን 18/03/2012 ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ጊዜዉ ያለፈዉ በዚህ ምክንያት መሆኑ ታዉቆ እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡ችሎቱም ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡ አድርጎ በሰጠዉ አስተያየት ፍርድ የተሰጠው በቀን 27/02/2012 ዓ/ም ሆኖ ስህተቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት የታረመዉ ተጠሪ ባቀረብኩት ማመልከቻ መነሻ ነዉ፡፡ አመልካች ይግባኙን በጊዜው ያላቀረበው በቸልተኝነት በመሆኑ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ፍርድ ከተሰጠበት ከቀን 27/02/2012 ዓ/ም ጀምሮ በመሆኑና የአመልካች ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ባለመሆኑ ማስፈቀጃዉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ችሎቱም በመ/ቁጥር 195771 ላይ በቀን 20/05/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሰጠዉ በቀን 27/02/2012ዓ/ም ሆኖ አመልካች የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበዉ በአገራችን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ሆኖ ዉሳኔ ከተሰጠ ከ77 ቀናት በኋላ በቀን 06/05/2012ዓ/ም በመሆኑና እርማት እየተሰጠ ለ21 ቀናት በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በመዘግየቱ ምክንያት ጊዜዉ አለፈብኝ በማለት ያቀረበዉ ምክንያትም እንደ በቂ ምክንያት ሊቆጠር የሚችል ስላልሆነ የአመልካችን ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም ሲል ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 12/06/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡-በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 መሰረት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እና ይርጋ ሊቆጠር የሚገባው ስህተቱ እርማት ተደርጎ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ሲገባ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የወሰነዉ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነዉ፡፡ጊዜዉ ያለፈብን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እርማት ለመስጠት ረጅም ጊዜ በመፍጀቱ ምክንያት ነዉ፡፡የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ መቆጠር ያለበት ዉሳኔዉ ላይ ያለዉ ስህተት ታርሞ ስህተት አልባ ዉሳኔ ከተሰጠበት ከቀን 18/03/2012ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ስለሚገባ በሰ/መ/ቁጥር 59085 ላይ ከተሰጠዉ ትርጉም አንጻር ጉዳዩ ታይቶ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲንችል አለመፈቀዱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባው ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው ወይስ ፍርድ ከታረመበት ጊዜ ጀምሮ ነው? እንዲሁም ፍርዱ ላይ ያለዉ ስህተት ከታረመበት ጊዜ አንስቶ ሲቆጠር ጊዜው አልፏል ወይስ አላለፈም የሚለው ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 14/08/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ፡- ዉሳኔዉ የተሰጠዉ በቀን

27/02/2012ዓ/ም ሲሆን የአጻጻፍ ስህተት እንዲታረም የጠየቅሁት ተጠሪ ነኝ ፡፡አመልካች ዉሳኔዉ እርማት ስላለበት ግልባጭ አልተሰጠኝም ያለዉ ምክንያት ለስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ምክንያት ስለሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡እርማቱም የፍርዱን መሰረታዊ ክፍል የሚነካ ባለመሆኑ አመልካች እርማቱን እየጠበኩ ጊዜ አለፈብኝ በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካች ይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበዉ በቀን 06/05/2012ዓ/ም ሲሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ነዉ ተብሎ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ ማስፈቀጃ ያቀረበዉ በቀን 11/01/2013ዓ/ም ነዉ፡፡ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ጉዳዩን በቸልተኛነት ባለመከታተል ጊዜዉን በአግባቡ ስላልተጠቀመና በሰ/መ/ቁጥር 59085 ላይ የተሰጠዉ ትርጉምም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ስለሌለዉ የአመልካች ማመልከቻ ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲችል እንዲፈቀድለት ያቀረበዉ ማመልከቻ ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራትና እና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ሊሆን ይገባል፡፡ይህም ሥርዓት የተዘረጋበት ምክንያት ክርክር ቀልጣፋ፣ ዉጤታማና ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሮች ተለይተዉ በሚታወቅ ሥነ ሥርዓት አግባብ ተመርተዉ ፍትሐዊ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ለማሳካት የታቀደዉ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለማድረግ ነዉ፡፡የይግባኝ አቀራረብ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ የተደነገገዉ ሥነ ሥርዓትም ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት በመሆኑ የሕጉን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 ስር እንደተደነገገዉ የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባዉ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ ከተሰጠጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 60 ቀናት ዉስጥ ነዉ፡፡የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ ማቅረብ እንዲቻል ለማስፈቀድ የሚቀርብ ማመልከቻ ጊዜዉ ሊያልፍ የቻለበትን በቂ ምክንያት የሚያሳይና ይህንኑ ምክንያት ከሚያስረዳ ማስረጃ ጋር መቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 325 እና 326 ስር ተደንግጓል፡፡ከእነዚሁ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ የምክንያቱ መከሰት በማስረጃ ከተረጋገጠ የምክንያቱ በቂ መሆን ያለመሆን ጉዳይ በእነዚሁ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ከግምት እየገባ እንደየምክንያቱ አይነት እየተመዘነ የሚወሰን ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ በቅን 27/02/2012ዓ/ም እንደሆነ አከራካሪ አይደለም፡፡በዚህ ዉሳኔ ላይ አመልካች ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ የተወሰነዉ የገንዘብ መጠን በአሃዝና በፊደል ሲጻፍ ልዩነት ስለነበር በፊደል የተጻፈዉ ስህተት ስላለበት በአሃዝ ከተጻፈዉ ጋር እንዲመሳሰል ተደርጎ እንዲታረም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ

መሆናቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ ስህተቱን የሚያርም ትእዛዝ የሰጠዉ በቀን 18/03/2012ዓ/ም ነዉ፡፡ ስህተቱ እንዲታረም ጥያቄ ያቀረበዉ አመልካች ባለመሆኑ ስህተቱን የሚያርም ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ ሳይጠብቅ ዋናዉ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይግባኝ ማለት እንደሚፈልግ ገልጾ ፍርድ ቤቱ ግልባጭ እንዲሰጠዉ መጠየቅ ይችላል፡፡ነገር ግን በዚህ አግባብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 323/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት በ60 ቀን ዉስጥ ይግባኝ እንደሚጠይቅ ገልጾ የዉሳኔ ግልባጭ እንዲሰጠዉ የጠየቀ ስለመሆኑና የሥር ፍርድ ቤት ግልባጩን ያዘገየበት ስለመሆኑ በመግለጽና በማስረጃ በማስደገፍ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አላስረዳም፡፡ እንዲሁም በፍርዱ ላይ ስህተቱ መኖሩን ካወቀም ራሱ ስህተቱ እንዲታረምለት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ  መጠየቅ እየቻለ ይህንን ስለማድረጉ አላስረዳም፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ አመልካችነት የአጻጻፍ ስህተት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ የታረመ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ይግባኝ የሚልበት ጉዳይ በስህተቱ ላይ ሳይሆን በፍርዱ ላይ ባለዉ ዋናዉ ጉዳይ ላይ እንደመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የአጻጻፍ ስህተቱን እስከሚያርም መጠበቅ ሳይጠበቅበት የፍርድ ዉሳኔዉ በራሱ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል በመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ ገልጾ የፍርድ ዉሳኔ ግልባጭ በመዉሰድ እስከ ቀን 27/04/2012 ዓ/ም ድረስ ባለዉ 60 ቀናት ዉስጥ ይግባኙን ማቅረብ ሲገባዉ የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበዉ በቀን 06/05/2012 ዓ/ም ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር 60 ቀን ካለፈ በኂላ ነዉ፡፡ በዚህ ቀን ያቀረበዉ የይግባኝ ማመልከቻ ጊዜ ያለፈበት ነዉ ተብሎ ተቀባይነት ሲያጣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 325/1 መሰረት ተቀባይነት የለዉም ተብሎ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ቀን ዉስጥ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉን ማቅረብ ሲገባዉ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉን ያቀረበዉ ግን ከወራት በኂላ በቀን 11/01/2013ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ የሚያሳየዉ አመልካች በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተቀመጠዉን የጊዜ ገደብ ንቁ ሆኖ አለመጠቀሙንና በግደለሽነት ማባከኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለዉ ፍርዱን የሰጠዉ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 208 መሰረት ይግባኝ በሚባልበት ፍርድ ላይ የሚገኘዉን ስህተት ካረመ በኂላ ሲሆንና በዚህ አግባብ እርማት እንዲደረግ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሳያልፍ ተጠይቆ የቀረበ አቤቱታ መርምሮ ፍርድ ቤቱ ተገቢዉን ትእዛዝ ሳይሰጥ ቢያዘገይ እና በዚህ ምክንያት ጊዜ በመባከኑ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ቢያልፍ ለይግባኝ ባይ እንደ በቂ ምክንያት ተቆጥሮለት የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻዉ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ግን ፍርዱ በራሱ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ሆኖ እያለ ፍርዱ ከተሰጠበት ከቀን 27/02/2012 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች በ60 ቀን ዉስጥ ይግባኝ ለማለት እንደፈለገ ገልጾ ግልባጭ እንዲሰጠዉ ጠይቆ በስር ፍርድ ጉድለት ምክንያት ጊዜዉ እንዳለፈበት ወይም የስር ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ያለዉን ስህተት የሚያርም ትእዛዝ ሳይሰጥ በማዘግየቱ ምክንያት ጊዜዉ እንዳለፈበት ካለማስረዳቱም በተጨማሪ ራሱ ያላቀረበዉን የእርማት አቤቱታ መሰረት በማድረግ ያቀረበዉ የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ በበቂ ምክንያትና ማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተቀባይነት በማጣቱ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

# ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 195771 ላይ በቀን 20/05/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም